# ፅናት

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን




ቅጽ 1 ቁጥር 5 ቅዳሜ ሚያዚያ 9 ቀን 2002 ዓ.ም ዋጋ 2 ብር

## ምዉስጥ ገጾች

• ታሪክ ራሱን . . . ገጽ 3
• «ሙስና» . . . ገጽ 4
• በፖለቲካ አቋም . .ገጽ6

# መድረክ የምረጡኝ ዘመቻውን እያጧጧፈ መሆኑ ተገለፀ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የ2002 ዓ.ም ምርጫን አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ፖሊሲዎቹን፣ኘሮግራሞቹን፣ ዓላማዎቹንና አንግቦት የተነሣውን አገራዊ ራዕይ የሚያንፀባርቁለትን በ500 ሺዎች የሚቆጥሩ በራሪ ወረቀቶችንና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ፎቶ ግራፎችና የምርጫ ምልክት የሆነውን አምስት ጣቶች የያዙ ፓስተሮችን ከአዲስ አበባ ውጭ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ማሠራጨቱን ከፓርቲው የሕዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ከተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተያያዘ ዜና የመድረክ አባል የሆነው አንድነት ፓርቲ ለቅስቀሳ ተግባር የሚውሉ 140 የድምፅ ማጉያዎችን ገዝቶ ለቅስቀሳ ለተሰማሩ አባላቱ ማከፋፈሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ የሚያመለክተ ውም መድረክ የ2002 ምርጫን በብቃትና በጥራት አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ታጥቆ የተነሣ መሆኑን ነው፡፡ የምርጫ ቅስቀሣው በክልሎች ምን እንደሚመስል በቅርቡ በደቡብ ኢትዮጵያ ሲንቀሳቀሱ ቆይተው የተመለሱትን አቶ ዳንኤል ሺበሺ ላቀረብንላቸው አጭር ጥያቄ ሲመልሱ፡-

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)






## መድረክ በመቱና ወልቂጤ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

***«ኢህአዴግ እኛን ለ19 ዓመት ስንሰማው እንጅ እሱ ሰምቶን አያውቅም»***

**የመቱ ሕዝብ**

ቅዳሜ ሚያዚያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም መድረክ በኢሊባቡር ዞን መቱ ከተማ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄዷልበእለቱ ስብሰባውን የመሩት ክቡር አቶ

ተመስገን ዘውዴ አና ክቡር አቶ አስራት ጣሴ እንዲሁም አስናቀ ሸንገማ ናቸው:

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## የመድረክ ዕጩ ተወዳዳሪ የመኪና አደጋ ደረሰባቸው



የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አባል እንዲሁም

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

# ምርጫችን በጃችን!!

# መልዕክተ ፅናት

## ፍጹምነት በሌለበት ፍጹም ዋስትና የለም

መድረክ በአለፉት ወራት በርካታ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን አካሄዷል፡፡ በእነዚህ ውይይቶች የተለመዱት የመክፈቻ ንግግሮች ከተደረጉ በኋላ ቤቱ ለአስተያየት፣ ለጥያቄና መልስ ክፍት ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ በተካሄዱ ስብሰባዎች ሁሉ ሳይነሳ የማይቀር አንድ ጥያቄ አለ፡፡ ይህም «ከዚህ በፊት አራት ፓርቲዎች ቅንጅት ነን ብለው መጡ፡፡ ደገፍናቸው፡፡ መረጥናቸው፡፡ ከዚያም አልፈን መስዋእትነት ከፍለን፡፡ በኋላ ግን ተበታተኑ፡፡ መበታተናቸው ልባችንን አቆሰለው፡፡ መንፈሳችን ተሰበረ፡፡ ዛሬ ደግሞ የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ መድረክ ነን ብላችሁ መጥታችኋል፡፡ እናንተም እንደተናንቱ ቅንጅት ለአለመበታተናችሁ ምን ዋስትና አለን? እንዴት እንመናችሁ ደግሞ ልባችን ለቆስል፤ መንፈሳችን ላይሰበር ምን ዋስትና አለን? የሚል ነው፡፡ ጥያቄው ከባድ ጥያቄ ነው፡፡ መልሱ ግን የሚመጣው ከአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከጠያቂም ከተጠያቂም በጋራ የሚመጣ ነው፡፡

የሰው ልጅ በባህሪዩ ፍጹም አይደለም፡፡ ፍጹም ያልሆነው የሰው ልጅ የሚፈጥራቸው ድርጅቶችም በባህሪ ያቸው ፍፁም ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ፍፁም ለአልሆነ አደረጃጀት ስለህልውናው ዋስትና መስጠት አይቻልም፡፡ ማድረግ የሚቻለው ያ ድርጅት በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ዛሬ ባይሳካ ነገ ይሳካል፡፡ መበታተን እንዳለሁ መሰባሰብም አለ፡፡በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መበታተንና መሰባሰብ አንድ አቢይ ክፍል የፖለቲካ ድርጅቶች በቅንነት መሰባሰብና መተባበር ተፈላጊ ዓላማ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ለመሳካቱ ተስፋ ሳይቆርጡ መታገል የግድ ይላል፡፡

በአንደኛው የዓለም ጦርነት የደረሰው የሰው ህይወት እልቂት፣ የንብረት ውድመትና የመንፈስ ስብራት እንደገና እንዳይደገም ሲባል አመፀኛን በጋራ ለመቋቋምና የዓለም ሠላምን የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ እንደ ኢ.አ በ1920 የዓለም መንግሥታት ማህበር (ሌግአፌኔሽን) ተመሠረተ፡፡

ሆኖም ከሃያ ዓመታት ያህል በኋላ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካስከተለወ ጉዳት በእጥፍ የባሰ ጉዳት በዓለም ላይ ደረሰ፡፡ የዓለም መንግሥታት ማህበርም ፈረሰ፡፡ ሆኖም የዓለም መንግሥታት ሕዝቦቻቸውን በእጥፍ እያደገ ከመጣ አደጋ ለማዳን እንደገና ከመሰባሰብና ከመተባበር የተሻለ ሌላ አማራጭ አልታያቸውም፡፡ የዓለም መንግሥታት ከመበታተን አልዳነም በማለት እንደገና ከመሰባሰብ ወደ ኋላ አላሉም፡፡ የአሁኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተ ጠናከረ መልክ መሠረቱ እንጂ፡፡ ይህ ድርጅት እንደ ዓለም መንግሥታት ማህበር ለአለመፍረሱ የተሰጠ ዋስትና የለም፡፡ አለ የሚባል ነገር ቢኖር ድርጅቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሰው ልጅ አእምሮ አቅም እስከፈቀደ ድረስ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ በዚህ ጥረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለስልሳ አምስት ዓመታት ቀጥሏል፡፡ በእነዚህ 65 ዓመታት ውስጥ ድርጅቱ በርካታ ፈተናዎች ገጥመውታል፡፡ ሶስተኛ የዓለም ጦርነት አሁንም ከሰው ልጅ ስጋቶች ዝርዝር ውስጥ አልተሰረዘም፡፡ እንዲያውም እ.አ.አ በ1960 ኩባን ማዕከል አድርጎ በአሜርካና በሶቪየት ሕብረት መካከል የተ ፈጠረው የኑክሊየር ፍንጭ ሶስተኛው የዓለም ጦርነት በቅርቡ እንዲያንዥብብ አድርጎት ነበር፡፡ የሶቪየት ሕብረት መሪ ዎች በወሰዱት ቆራጥ ርምጃ ተወገደ እንጂ፡፡ መድረክ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያለው አማራጭ አሁንም ተስፋ ሳይቆርጡ ጠንክሮ መታገል ነው፡፡ በዚህ ትግል ሕዝቡ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ሚናው የዳር ተመልካች፣ የሩቅ ተቺና ወቃሽ መሆን አይደለም፡፡ የጉዳዩ ባለቤት እንደመሆኑ የድርጅቱን እንቅስቃሴ በቅርብ በመከታተል ቀጣይነቱን አስተ ማማኝ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት፡፡ ለሕብረቱ መዳከም ምክንያት የሚሆን አዝማሚያ የሚያሳይ ወገኖችን በቅርብ የመከተል፣ የመምከር፣ ከዚያም አልፎ የመገሰጽ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ነው በመገቢያችን ላይ ስለተነሳው ተደጋጋሚ ጥያቄ መልስ ሰጪው ተጠያቂው ብቻ ሳይሆን ጠያቂም ጭምር ነው ያልነው፡፡ ከዚህ በፊት የተደረጉ መበታተኖች ትክክለኛ ምክንያታቸው ምን እንደሆነ፣ የምክንያቱ ምንጮች እነማን እንደሆኑ በግልጽ የማስቀመጥ ባህላችን የዳበረ አይደለም፡፡ ስለዚህ ነገሮች ተደብስብሰው ያልፋሉ፡፡ በዚህ የተደበሰበሰ ሁኔታ አጥፊ ወገን በሕዝብ እጅ ተገቢውን ሳያገኝ ያልፋል፡፡ ችግሮች ሳይፈቱ ወደፊት ይኬዳል፡፡ ውጤቱም ከችግር ወደ ችግር በመሔድ በጤናማ መንገድ ለመቀበል አለመቻቻል ነው፡፡

ስለዚህ ለአንድ ድርጅት ጤናማ በሆነ መንገድ ለማስቀጠል አንዱ ወሳኝ ሁኔታ ግልጽነት ነው፡፡ ግልጽ ውይይት ፤ ግልጽ አሠራር፡፡ ሲኖር ችግሮች ካሉ ግልፅ ሆነው ይወጣሉ፡፡ ግልጽ ሆነው ከወጡ ምክንያቶቻቸው ምን ወይም ማን እደሆነ ይታወቃሉ፡፡ ሕዝብ ዳግም ምክንያቱ ለታወቀ ችግር መፍትሔ መሻት አይቸግረውም፡፡ መድረክ በግልጽ ውይይት፣ በግልጽ ተግባር ከሕዝብ ጋር በቅርብ በመሥራት ቀጣይነቱን ይበልጥ ያጠናክራል፤ አሸናፊነቱንም ይበልጥ አስተማማኝ ያደርጋል፡፡

# መልዕክቶቻችሁ

## ለወጣት አንዱዓለም አራጌ

ከሁሉ በፊት ሠላምታዬን አቀርባለሁ፡፡ከሠላምታየ በኃላ ላሳስብህ የምወደው

1. በየቤተክርስቲያኑ ዙሪያ መጽሐፍ የሚነገዱና ፣አርከበ ሱቅ እየተባለ የሚጠራው ሱቅ የሚሠሩ ጫማ ጠራጊዎች
2. የመጫንና የማውረድ ሸክም የሚሠሩቱን የኢሕአዴግ ካድሬ ዎች በየቀበሌው እየሰበሰቡ ኢህአዴግን ካልመረጣችሁ ሥራ መሥራት አትችሉም እያሉ እያስፈራሩዋቸው ነው፡፡ እንዲያውም መጽሐፍ ነጋዴዎችን ምርጫው ሲደርስ እናየዋለን በማለታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤ/ክርስቲያን ዙሪ ያ መጽሐፍ ዘርግተው የሚነግዱት በሙሉ ተከልክለዋል፡፡ እነመርጣለን ብላችሁ ቃል ከገባችሁ ግን እንፈቅዱላቿለን በገንዘብ በልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ሕዝብን በመደለል ላይ ስለሚገኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን ነፃነቱን የሀገሩን ድንበር ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ እንደማይሸጥና እንደማይለውጥ ከጥንት አባቶቻችን ታሪክ ጋር በማያያዝ በማገናዘብ በየስብሰባችሁ ለሕዝብ በቂ ግንዛቤ እንዲገኝና የስነ ልቦና ትጥቅ እንድታስታትቁት በትህትና አሳስባለሁ፡፡ በተራ ቁጥር 1ና 2 ለፃፍኩትም ሙያ በልብ መሆኑን የሀገርና የነፃነት ጉዳይ መሆኑን አስረዷቸው፡፡

ሌላው መጋቢት 12 ቀን ባደረጋችሁት ስብሰባ ሕገ መንግስቱ ያስቀመጠውን አንቀጽ 29 በተለይ አንተ ያሳዝነኛል ስትል ነበር፡፡ ታዲያ ለምንድ ነው ሕገ መንግስቱ የሰጠውን መብት አንዱ ተናጋሪ ሀሳባቸውን ሳይጨርሱ ማስቆማቸው ምናልባት ብንሠማው ኖሮ መልካም ነበር መድረኩን መቆጣጠር ያለባችሁ እናንተ እንጂ ተሰብሳቢወ አይደለም፡፡ የማይፈለጉት ስም ስለተጠሩ የሰውን ሀሳብ መቁረጥ አይገባምና ይታረም፡፡

ሻለ አምላክ ተስፋዬ ከአ.አ ኮተቤ ክ/ከተማ

## መድረክ ሲያሸንፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!!


# ፅናት

በአንድነት ፓርቲ ኤዲቶሪያል ቦርድ የምትታተም በፖለቲካዊ፣ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩራ በ15 ቀን አንዴ የምትወጣ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

አንዳርጌ መሥፍን (አድራሻ :የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 የቤት ቁጥር (አዲስ)

ስ.ቁ 0913 05-69-42

ሪፖርተር: ዳንኤል ተፈራ

ስ.ቁ :-0911 035035

የኮምፒውተር ጽሑፍ:- ትግስት ቦጋለ

ሷ.ቁ 1910 142316

**አታሚ**

ሆራይዘን ማተሚያ ቤት

**አድራሻ**

ቂርቆስ ክ/ከተማ

**ቀበሌ**

17 የቤ.ቁ 124

**የአሳታሚው አድራሻ**

ቂርቆስ ክ/ከተማ

ቀበሌ 31 የቤት ቁጥር 461 ባምቢስ ሱፐር ማርኬት ፊት ለፊት

# ፖለቲካ

# «ታሪክ ራሱን ይደግማል»

መድረክ

ታሪክ እራሱን ይደግማል ይባላል:: እውነትም ታሪክ እራሱን ይደግማል እውነታነቱን ለማረጋገጥ ብዙ መጓዝ አያስፈልግም:: የሀገራችን የ30 ዓመት ግድም ታሪክ በቂ ማስረጃ ይሆነናል:: ለምሳሌ ብለን ለመነሳት ከሀገራችን ታሪክ ሁለት አንጐዎችን እንውሰድ:: የካቲት 1966 እና ግንቦት 1983ን:: እነዚህን ሁለት የታሪክ አንጎዎችን ስንመለከት አንዱ የሌላው ምስል እየተንፀባረቀበት እናገኛቸዋለን:: የካቲት 1966 ለዘመናት የታመቀ የሕዝብ ትግል መጨረሻ ይመስል ነበር፤ ግን አልሆነም :: በአንፃሩ ግን ይህ ሕዝባዊ ትግል መጨረሻው ምዕራፍ ደረሰና ሕዝብ እንደቀድሞ መገዛት አለመፈለጉ ሳይሆን አለመቻሉ ተከስቶ ሕሌናዊና ነባራዊ ሁኔታ ሳይሰካ በተፈፀመ ሕዝባዊ አመፅ የኃይለ ሥላሴ ግባተ ታሪክ ታወጀ፤ የተከተለው ወታደራዊ መንግስት ነበር:: «ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም» የሚለውን ማራኪ መፈክር አንግበን ተነሳን ያሉት ጥቂት ምርጥ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረግተኞች ቃላቸውን ለማጠፍ ወራት አልፈጀባቸውም፤ ምድሪቱን የደም አበላ እንዲወርድባት አደረጓት::

ይህም ለ17 ዓመት የዘለቀ የአገራችን ታሪክ ሆነ:: ይህ ታሪካችን መደማመጥ የጠፋበት ርስ በርስ ተነጋግሮ መግባባት እስከ ወዲያኛው የተዘነጋበት ወንድም በወንድሙ ላይ ሰይፍ የሳለበት ዘመን ነበር::

ሁለተኛው የታሪክ አንጓ ከዚህ የ17 ዓመት የአደፈ ታሪካችን በኋላ የቀጠለውና የግንቦት 20ን የዴሞክራሲ ተስፋ እነሆ ያለን ነበር:: ሁላችንም ይህንን የነፃነት፤ የዴሞክራሲና የእኩልነት ተስፋ አሜን ብለን ተቀብለን አደባባይ የወጣንበት ጊዜ ቢሆን ይህው ግንቦት 20 መሆኑን የሁላችንም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: ይሁንና ተስፋ በተስፋነቱ ብቻ እየመከነ በተግባር ሳይገልፅ ዛሬ የደረሰንበት ተጨባጭ ሁኔታ ለይ እንገኛለን:: ዛሬ ዛሬ አንዳችን የሌላውን ብሔል ማዳመጣችን ቀርቶ የራሳችንን ብቻ ስናልመዘምዝ ውለን የምናድር የሌላውን ጩኽት የቁራ ጩኽት አድርገን የምንቆጥር ሆነናል::

የመቻቻል ፖለቲካ ደብዛው ባልነበረበት የዚያ ትውልድ አባላት እርስ በእርስ በአደባባይ የሚፋጅበት የነበረው ዘመን እንደገና አለሁ ደረስኩ ያለን ይመስላል:: ለዚህም ነው ታሪክ እራሱን ይደግማል ያልነው:: እውነትም ታሪክ እራሱን ይደግማል::

ዛሬ ዴሞክራሲ ነፃነትና ከግለሰብ መብት ጀምሮ የቡድን መብት ይከበርበታል በሚባለው ሀገራችን የሚባለውና የሚደረገው ለየቅል ሆኗል:: መንግስትና የመንግስት ሥልጣን የጨበጠው ኤሕአዴግ የሚፈልገውና የገጠመውን ሲያውድስ፤ ሲመርቅና ሲያከብር የጠላውንና እኔን አይደግፍም የሚለውን ሲያውግዝና ሲያብጠለጥል ይታያል:: ይህ 1997 ታሪካዊ ምርጫ በኋላ እየተሻሻለ ሳይሆን እየሰፋ እያስፈራራና እያስገመገመ የሊማሊሞ ገደል ሆኖብናል::

የዚህ ዕጣ ከደረሰባቸው መካከል በጠንካራ ተቃዋሚነቱ በዓለም ዙሪያ ሳይቀር ታውቆ በታሪክ አደባባይ ብቅ ያለው ድርጅታችን መድረክ አንደኛውና ዋንኛው ሆኖዋል:: ይልቁን ከውግዘትና ከማብጠልጠል ባሻገር አባላቱ እየታሰሩና እየተሰደዱና አልፎ አልፎም የመድረክ አባል በሆነው አረና ላይ እንደተፈፀመው የሕይወት ዋጋም ጭምር እየከፈሉ ይገኛሉ::መድረክ እንደመድረክ በተንቀሳቀሰበት አጋጣሚዎች ሁሉ የክርስትና ሥም እየወጣለት፣ ያለ ተግባሩ ተግባር እየተፈጠረለት፤ በመንግስት መገናኛ ብዙሃንና መሰል ተግባር እንዲፈፅሙ በተደራጁ ኢህአዴግ ሠራሽ ሚዲያዎች ጥላሸት ሲቀባ ውሎ ማደሩ የተለመደ ሆኖል::

የስያሚዎቹን ብዛት በቁጥር ለመግለፅ የሚያታክት ቢሆንም ከብዙ በጥቂት ለመጥቀስ «የጥፋት ኃይሎች ግንባር፣ የኒዎ ሌበራል ወኪሎች» እየተባልን በየአደባባዩ ስንወገዝ መደመጡ ተለምዶዋል:: በፖርለማ ሳይቀር «መድረኮች ከጎዳና የተሰባሰቡ ናቸው:: አባላቶቻቸውም በሙስና ታስረው የወጡ ሙስኞች ናቸው» እየተባልን የመርገም ጨርቅ እየለበሰን ነው:: በጣም የሚገርመው ደግሞ የመከላከያ ኃይላችንን የመተንኮስ ተግባር ፈፅማቸኋል መባላችን ሲሆን እኛ ግን የሃገራችን ዳር ድንበር በመጠበቅ ላይ የሚገኘው የመከላከያ ኃይላችን የራሳችን ልጅ፣ ወንድም፣እህትና ወገን ስብስብ መሆኑን የምናምን የዜግነት ኃላፊነት የሚሰማን ሕዝባዊ ወገኖች መሆናችንን ማረጋገጥ እንወዳለን::



በሌላ በኩል እንደ ብርቱካን ያሉ የሕሌና እስረኞች ጉዳይ ከአያያዛቸው ጭምር እያሳሰብን የመጣ ጉዳይ ነው:: የወ/ሮ ብርቱካን የጤንነት ሁኔታም አሳሳቢ ደረጃም መድረሱ ይሰማል:: በመሆኑም ድርጅታችን በዚህ አጋጣሚ ወ/ሮ ብርቱካን እንደ ቀይ መስቀል ባሉ ገለልተኛ ወገኖች የሕክምና ዕርዳታ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች ለሚመለከተው አካል ጥያቄአችንን እናቀርባለን:: ከዚህ ባሻገር ዛሬ ባለንበት አጠቃላይ ሁኔታ አባላቶቻችንን በሚመለከት ምንም ዋስትና በሌለበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን ማለት ይቻላል:: ይልቁንም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፖርላማ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር «በምረጡኝ ቅስቀሳ የሚነገሩ መረጃ የሌላቸው ህገ ወጥ የሚባሉ አባባሎች ከምርጫ በኋላ የሚያስከስሱና የሚያስጠይቁ ይሆናሉ» በማለታቸው ስጋታችን እጥፍ ድርብ ሆኖ በውስጣችን አለመረጋጋት ፈጥሮብናል:: ከዚህ ሌላ በተለያዩ አካባቢዎች በአባላቶቻችን ላይ ድብደባ ፣ ዛቻና ማስፈራራት የመሳሰሉ የምርጫውን የስነ ምግባር ደንብ የሚፃረሩ ተግባራት እየተፈፀሙባቸው ይገኛል:: ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ

1. በደቡብ ሃዲያ ዞን ዱና ወረዳ፤ አንሻና ውሃ ገበታ ቀበሌ ፤ ቡራ ቡራሻና ቀበሌ በኢናራ ቀበሌ ምንም ዓይነት

2.ምዕራብ ወለጋ ዞን በ27/07/2002 ዓ.ም የአባላቶቻችን የተፈቀደ ስብሰባ ብጥብጥ መልክ እንዲበተን ተደርጓል::

3.በዚሁ በምዕራብ ወለጋ ዞን ነጆ ከተማ በ28/07/2002 ዓ.ም ተመሳሳይ ብጥብጥ ተካሄዶ አባላቶቻችን በአዳራሽ ውስጥ የጀመሩት ስብሰባ ተበትኗል:: በወቅቱ በጥባጮች ከፖሊስ አቅም በላይ የሆነ ችግር ፈጥረዋል ተብሎ ምንም ዓይነት የህግ ከለላ ሳይደረግላቸው ቀርቷል:: በሌላ በኩል ጉቴ ኑሌ ካባ ቁጥር 2 የምርጫ ክልል ስዩ ገበሶ በሚባል ወረዳ ውስጥ አስመስሎ በተዘጋጀ የኦፌድን ማዕተም ግብር አትክፈሉ የሚል መንግሥትንና ድርጅታችንን የሀገሪቱን ህግ የሚያላትም ተግባር ተፈፅሞ በዚሁ ሳቢያ በርካታ የኦፌድን አባሎች ያልፈፀሙትን ተግባር ፈፅማችኃል በመባል በቁጥጥር ስር ውለው በምርመራ ላይ ይገኛሉ:: በዚህ ደበሶ ከተማ 24/07/2002 ዓ.ም ምሽት የድርጅታችን የኢሕአዴግ አባል በሆነው ደገፋ ረጋሳ የመኖሪያ ቤት በር ላይ መፈክር ለመለጠፍ ሙከራ ሲደረግ አባሉ አባል ያልሆንኩበት ድርጅት መፈክር በሬ ላይ አይለጠፍም በማለቱ እስከ ዛሬ ተይዞ በስር ላይ ይገኛል::

4.በሃዲያ ዱና ወረዳ ውስጥ ድብደባ የደረሰባቸው አባላቶቻችን 1ኛ/ አቶ ተስፋዬ ቡቂ የክልል ዕጩ ተወዳዳሪ 2ኛ/ አቶ ዳዊት ለገሰ 3ኛ/ አቶ አየለ ቡፌቦ ናቸው:: እነዚህ ግለሰቦች እጅና እግራቸው ተሰብሮ የአልጋ ቁራኛ ሆነዋል::

5.በ24/07/2002 ዓ/ም በናራ ቀበሌ የክልል ዕጩ የሆኑት አቶ ታደሰ ቤንጫሞ አቶ አንጼሙ ዘውዴ እንዲሁም የተወካዮች ምክር ቤት ዕጩ አቶ አጫሙ ቦቄ የድብደባ ወንጀል ተፈፅሞባቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ተግባራት ሆን ተብሎና ታቅዶ አባላቶቻችንና ዕጩዎቻችን ከአላማቸው ውጩ ለማረግ የተፈፀመ ህገወጥ ተግባራት መሆናቸው ግልፅ ነው::

6.በአንዳንድ ከተሞች የተቃዋሚዎች በተለይም የመድረክን እንቅስቃሴ ለመግታት ሰዓት እላፊ እስከ ማወጅ ተደርሷል::

በአጠቃላይ በመላ ሀገሪቱ የመንግስት ሠራተኞች በሚመለከት ለምርጫ ቅስቀሳ ሥራ ከመጠቀም ተጧጡፎ ቀጥሏዋል:: እንደ ማስረጃ የተዘጋጀውን ፎርም አግኝተን በእጃችን ይገኛል:: ኢህአዴግ የቅስቀሳ ስራዎችን ለመስራት የመንግስት ንብረት በሆኑ እንደ መኪና ባሉ ቁሳቁሶች መጠቀሙ የተለመደና ተራ ነገር እየሆነ መጥቷል:: በአጠቃላይ የአለንበት ሁኔታ መንግስት እንደ መንግስት ምርጫውን በገለልተኝነት መመልከት አልቻለም:: በአንዳንድ አካባቢዎች ኢህአዴግን አለመምረጥ እንደ ሴፍቲኔት ባሉ የዕርዳታ መረቦች አካቶ ከዕርዳታ ከማግኘት ወጪ የረጋል እየተባለ ማስፈራሪያና ዛቻ ይሰራጫሉ:: ኢህአዴግን አይመርጡም ተብሎ በተገመቱ ሰዎች ላይ የሚፈፀመው የማግለል ተግባር ለሌሎች እንደመቀጣጫ ሆኖ የተዘጋጀ ነው ማለት ይቻላል:: ከማግለሉ ባሻገር ጠንክረው እንቢተኛ ወደሆኑ ግለሰቦች ሽማግሌ የመላክ በጥርነፋ የሕዝብ ሰንሰለት ውስጥ እንዲገቡ ማስገደድ ኢህአዴጋዊ

(ወደ ገፅ 5 ዞሯል)

# መድረክ የምረጡኝ . . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

44 የድምፅ ማጉሊያዎች፣50.000 የመድረክ አምስት ጣቶች ያሉበት በራሪ ወረቀቶችንና 3500 ፖስተሮችን በመውሰድ ለወረዳ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማከፋፈላቸውንና የሕዝቡ ስሜትም ይሆነኛል ያለውን ዕጩ ለመምረጥ የተነሣሣ መሆኑን ለማወቅ እንደቻሉ አስረድተዋል:: ሌላው የተደነቁበትን ሲገልፁልን በርካታ ወጣቶች የመድረክን የምርጫ ምልክት የሆነውን አምስት ጣቶች በባጅ መልክ አሠርተው ባንገታቸው አጥልቀው ማየታቸውንና ይህም የሕዝቡን የለውጥ ፈላጐት የጋለ መሆኑን የሚገልፅ ነው ሲሉ መገረማቸውን ገልፀው በቀጣይም በወላይታ ሶዶ ፣በቁጫ፣በሳውላ፣ በዳወሮ፣በአርባምንጭና በጅንካ ትላልቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ለማካሄድ በዝግጅት ላይ እንዳሉ አቶ ዳንኤል ሺበሺ አክለው ገልፀዋል::

በተያያዘ ዜና ከዚህ አዲስ አበባ ሁለት ሕዝባዊ ስብሰባዎች ሚያዝያ 3 ቀን 2002 ዓ.ም ተካሄደዋል:: አንደኛው ከሰዓት በፊት ፈረንሣይ ለጋሲዮን በሚገኘው የካራማራ የሙያና የቴክኒክ ት/ቤት አዳራሽ ውስጥ ሲሆን አብዛኛው

ተሰብሳቢ ትኩሱ ኃይል ወጣቱ ነበር:: ስብሰባውን በክብር እንግድነት በንግግር የከፈቱት የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀመንበርና የጥናትና ምርምር ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ነበሩ:: ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በንግግራቸው መግቢያ ላይ ከልጅነታቸው ጀምረው እስከ 72 ዓ.ም ድረስ በፈረንሣይ ለጋሲዮን አካባቢ ይኖሩ እንደነበር ገልፀው «ዛሬ በመሀከላችሁ ተገኝቼ ንግግር እንዳደርግ በመታደሌ የተለየ ትዝታ፣ የተለየ ስሜትና የተለየ ክብር ይሰማቸዋል» ሲሉ ከተሰብሳቢው ሕዝብ የሞቀ ጭብጨባ ተችሯቸዋል:: ከዚያም ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ወደ ልጅነት ሕይወታቸው መለስ ብለው ውትድርና ገብተው በሲግናል ለሶስት ዓመታት ያህል ስልጥነው እንደነበርና ሕይወት ጠመዝማዛ ነችና ከውትድርና ወጥተው ለዶክትሬት ደረጃ መድረሳቸውን ሲገልፁ ተሰብሳቢው በመገረም ነበር ያዳመጣቸው :

ከዶ/ር ኃይሉ የመግቢያ ንግግር ቀጥሎ በኘሮግራሙ መሠረት የዕጩዎች ተወዳዳሪዎች ትውውቅ ቀጥሎ ዕጩዎች ለሚመርጣቸው ሕዝብ የትምህርት ደረጃቸውን የሥራ ልምዳቸውንና የፖለቲካ ተሣትፏቸውን አስተዋውቀዋል:: በመጨረሻም ለጥያቄና አስተያየቶች መድረኩ ክፍት ሆኖ ከቤ

አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ተደጋጋሚዎችና በየጊዜው የሚጠየቁ የሥጋት ጥያቄዎች ነበሩ:: ለምሳሌ «መድረክ እንደ ቅንጀት ላለመፍረሱ ምን ዋስትና አላችሁ? ኢሕአዴግን በምርጫ ብታሸንፉት እንደ 97 ዓም ሥልጣን አለቅም ቢል እናንተ የምትወስዱት ርምጃ ምንድን ነው?--»የሚሉ ይጉኙባቸዋል::ከመድረክ በቂና አጥጋቢ መልስ ተሰጥቷል:: ለየት ያሉና አዝናኝ የሆኑ አስተያየቶችም ተሰንዝረው ተሰብሳቢውን ሕዝብ «ማሽላ ሲያር ይስቃል» እንዲሉ አስውቆታል:: ለምሳሌ ያህል ከቀረቡት ውስጥ:

« ሁለት ጓደኛሞች በከተማ አውቶቢስ ሲጓዙ አንደኛው ጓዴ 66 ዓ.ም ተኝቼ በህልሜ ንጉሡ ከሥልጣን ሲወርዱ አየሁ ወረዱ:: በ83 ዓ.ም ደግሞ ተኝቼ በህልሜ ደርግ ከሥልጣን ሲወርድ አየሁ:: እሱም ወረደ አለና ዝም አለ:: ጓደኛው ለመስማት በመጓጓት «ጋዴ ጥሩ ጥሩ ህልሞችን አይተህ ኖሯል:: ለመሆኑ ስለኢሕአዴግስ ሕልም አላየህም?» ሲል ጠየቀው:: « አይ ጓዴ! ኢሕአዴግማ መቸ አስተኛን!» ሲል ተሰብሳቢው በሣቅ አወክቷል:: ሌሎች ተመሳሳይ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ቀርበው በቂ መልስ ከተሰጠባቸው በኋላ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ሰብሳባው ተጠናቋል::

ሁለተኛው ሕዝባዊ ስብሰባ የተካሄደው ከሰዓት በኃላ ሲሆን የተካሄደውም ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በሚወዳደሩበት በወረዳ 23 ቀበሌ 06 አዳራሽ ውስጥ ነበር:: የክብር እንግዳው የወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር የተከበሩ ኘ/ር በየነ ጴጥሮስ ናቸው:: ኘ/ር በየነ በንግግራቸው ወቅት ስለመድረክ አመሠራረትና ዓላማ በስፋት ካተቱ በኋላ ስለምርጫው ሁኔታ ሲያብራሩ የኢሕአዴግን እኩይ ተግባር ሲገልፁ «ኢሕአዴግ ራሱን ከሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲል የምርጫውን ሂደት በማጭበርበር ጀምሮ የተለያዩ አፈናዎችን እንደሚያካሄድ ጥርጥር የለውም» ካሉ በኃላ « እኛ እጅ ከፍንጅ ይዘን እናውቃለን እኛ ኮሮጆ ሲገለበጡ ይዘን እናውቃለን:: እኛ የድምፅ ቆጠራን ሲያጨበረብሩን እናውቃለን:: ግን ኢሕአዴግን የምንጠይቀውና የምንመክረው የሕዝብን ፈቃድና ይሁንታ ሣታገኝ አገር መግዛት አትችልም ነው::» በማለት በምሬት ገልፀው በመቀጠልም ከሰሞኑ የኢሕአዴግ ጥቃቅን ካድሬዎች ቤት ለቤት እየዞሩ

አንድ ላምስት በሚል መርህ እየፈጠሩ ያሉትን ትርምስ እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል::«--- አንድ ሰው ቢያንስ አምስት ሰዎችን ቤት ለቤት እየዞረ ስም፣ የቤት ቁጥር፣ ለምርጫ የተመዘገቡበትን የካርድ ቁጥር ከመዘገቡ በኃላ የኢሕአዴግ የምርጫ ምልክት ንብ መሆኑን አስረድተው ግለሰቡን/ግለሰቧን አስፈርመው ኢሕአዴግን ባትመርጡ በፈርማችሁት ፊርማ መሠረት ትጋለጣላችሁ ወይንም ርምጃ ይወስድባችኃል በማለት ሕዝባችን የስነ ልቦና ስለባ እያደረጉት ነው» በማለት በምሬት ከገለፁ በኋላ አያይዘው « ይህ ስሌትም ኢሕአዴግ 4 ሚሊዮን አባላት አለኝ አንዱ አባሌ 5 ሰዎችን ቤት ለቤት እየዞረ ቢያስፈርም ከተመዘገበው 27 ሚሊዮን መራጭ መሀከል 20 ሚሊዮን መራጭ አገኛለሁ በማለት ነው:: ይህ አይነቱ አሠራረና አካሄድም የሥነ-ምግባር ጥሰት ብቻ ሣይሆን የሕግ ጥሰትም ነው:: ሕዝባችን በዚህ የቤት ለቤት ዘመቻ እየተስፈራራና እየተዋከበ ኢሕአዴግን ካልመረጥክ እየተባለ ቅድመ ዛቻ እየተካሄደበት ነው:: የሆነ ሆኖ ሕዝባችን የፈለገውንም ያህል መስፈራራት ቢካሄድበትም ያሰበውን ከመምረጥ ወደ ኋላ አይልም:: በመሆኑም ባለ አምስት ጣቶች ምልክት የሆነውን መድረከን ይመርጣል!!» በማለት ቀኝ እጃቸውን ወደ ላይ በማንሣት ወደ ሕዝቡ ሲያሳዩ ሕዝቡ በበኩሉ እጆቹን ወደ ላይ በማውጣት የሞቀ ድጋፉን ሰጥቷቸዋል::

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በበኩላቸው ወረዳ 23 የሚኖሩበት እንደ ሆነ ጠቅሰው በ97 ምርጫ ግን ወረዳቸውን ለኢ/ር ኃይሉ ሻወልና ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ለቀው በወረዳ 10 ተወዳድረው ኢሕአዴግን 30 ሺ ለሶስት ሺ አሸንፈውት እንደነበር አስታውሰው በ2002 ምርጫ ደግሞ የወረዳ 23 ሕዝብ እንደሚመርጣቸውና ተመሣሣይ ውጤት እንደሚያስመዘግቡና የወረዳቸው ድምፅ እንደማይነፍቃቸው በርግጠኝነት ሲናገሩ ከሕዝቡ የሞቀ የድጋፍ ጭብጨባ ተችሯቸዋል::

በመጨረሻም በተያዘው ኘሮግራም መሠረት ዕጩዎች ራሳቸውን ካስተዋወቁ በኃላ ከሕዝቡ የቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ተሰጥቶባቸው የስብሰባው ፍፃሜ ሆኗል::

# በመቱና ወልቂጤ . . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

መድረክ ለከተማው ህዝብ የ2 ቀን ቅስቀሳ ቢያደርግም በተቃራኒው የገዥው መንግስት ካድሬዎች የቀበሌ ተጠሪዎች በህዝብ መውጫና መግቢያ በር በመቆም ስብሰባው እንዳይሳካ ቢሞክሩም ወደ 500 ህዝብ በስብሰባው ተገኝቷል:: የእለቱ ስብሰባ ልዩ የሚያደርገው በስብሰባው የተገኘው ህዝብ ሁሉ በአንድ ስሜት የመድረክ ፓርቲ ደጋፊ መሆኑ ነበር::

**በእለቱ ከተሰብሳቢው ከተነሡ አስተያየቶች**

1. የኢህአዴግ ተወካይ ጥያቄ ለመጠየቅ ለመድረክ አስተባባሪ መድረክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የመድረኩ አስተባባሪዎች ለኢህአዴጉ መድረኩን ሰጡት ቢሆንም ተሰብሳቢው ሕዝብ ግን እኛ ኢህአዴግን ለ19 ዓመት ስንሠማው እንጂ እኛ የምንለውን ሠምቶ አያውቅም:: ስለዚህ እድል አንሰጠውም በማለት ተሰብሳቢው መልስ ሰጥቶዋል::
2. በ2002 አገር አቀፍ ምርጫ ኢህአዴግ ለምረጡኝ ቅስቀሳ የአየር ጊዜ ማጥፋቱ ተገቢ አይደለም:: ምክንያቱም የ19 ዓመት እያየነው ለምን ጊዜውን ያጠፋል በማለት ተሰብሳቢዎች አስተያየት ሰጥተዋል::
3. ኢህአዴግ ከ1997 ዓ/ም ወዲህ ልማት ጀምሬያለሁኝ ይላል:: ነገር ግን በመቱ ከተማ ውሰጥ ገጠሩንም ጨምሮ የምናየው ሚ/ር ካርል የሠራውን ሆስፒታልና ጤና ጣቢያ ብቻ ነው:: ስለዚህ ኢህአዴግ የሚነግርን አዲስ ራዕይ የለም:: ሲል የስብሰባው ታዳሚ በአንድ ድምፅ ጠይቃል::

በተያያዘ ዜናም በማግስቱ እሁድ በወልቂጤ ከተማ ጉራጌ ዞን ሕዝባዊ ስብሰባ ተደርጓል:: በዞኑ ዋነኛ የኢህአዴግ ተፎካካሪ ነው ሲሉ የስብሰባው አዘጋጆች ገልፀዋል:: እሁድ ሚያዚያ 3 ቀን 2002 ዓ.ም የመድረክ አመራር አባላት የሆኑት አቶ አንዱአለም አራጌ ኘ/ር መራራ ጉዲና እንዲሁም በርካታ የአንድነት ወጣቶችን በመያዝ 4 ሰዓት ላይ ወልቂጤ ከተማ ደርሰዋል::

ስብሰባውን የመሩት የተከበሩ አቶ በቀለ ወ/ሚካኤል ናቸው:: የተካሄደው ወልቂጤ ሁለገብ አዳራሽ ሲሆን የከተማው ኗሪ በተለይም ወጣቱ አዳራሹን ግጥም አድርጐ እንደነበር አስተባባሪዎች ገልፀው የመግቢያ ንግግር በኘ/ር መራራ ጉዲና አቅርበዋል:: እንዲሁም የሴቶች አቋም በወ/ሪት ልዕልና ጉግሳ ቀርቧል::

በዕለቱ አስገራሚ ጉዳዮችም ታይተዋል ያሉት አዘጋጆቹ ከነዚህም ውስጥ ገዥው ፓርቲ በካድሬዎቹ አማካኝነት ጥያቄ ተፅፎ ተስጥቷቸው የገቡ የነበሩ ሲሆን በካድሬዎች ተጽፎ የተሰጣቸው ጥያቄ አስቀድሞ ለመድረኩ መሪዎች ደርሷቸው ኖሮ ከጠያቂዎች መሀከል አንዷ እጃን በማውጣት ሲፈቀድላት የተሰጣትን ጥያቄ ማንበብ ስትጀምር ከመድረኩ «እህታችን ከንቱ አትድከሚ እኛ እናንብልሽ » ብለው ይዛው የቀረበችውን ሲያነቡላት ተበሳጭታ አዳራሹን ለቃ ስትወጣ አባሪዎቿም ተከትለዋት መውጣታቸውን ከስፍራው የነበሩ ድራማውን የተከታተሉ ተርከውልናል:: በመጨረሻም የመዝጊያ ንግግር በአቶ አንዱአለም አራጌ ተካሂዶ ስብሰባው ተጠናቋል::

## የመድረክ ዕጩ. . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ አቶ ዳዊት አሰራደ በሚወዳደሩበት የፈኖተ-ሰላም አካባቢ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የትንሳኤ በዓልን ለማክበር እና ከመራጩ ህዝብ ጋር ለመወያየት ከአዲስ አበባ ወደ ፍኖተሰላም ከተማ ሲያቀኑ እንጦጦ አከባቢ በደረሰ የመኪ ግጭት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል:: አቶ ዳዊት አሰራደ በፍኖተሰላም አካባቢ የምርጫ ክልል የጃቢጠናን ወረዳ ለተ/ም/ቤት የመድረክ ዕጩ ተወዳዳሪ ሲሆኑ ምርጫውን በአሸናፊነት ለመወጣት በወረዳው ከፈተኛ የቅስቀሳ ስራ መስራታቸው ታውቋል::

የደረሰባቸው አደጋም በግራ እግራቸው ላይ የመቀጥቀጥ በቀኝ እግራቸው ላይ ስብራትና ግንባራቸው ተፈንክቶ ዮርዳኖስ ሆስፓታል ርዳታ እየተደረገላቸው ይገኛል::

# ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ

## « ሙስና»

**ከአንዳርጌ መስፍን**

ዛሬ በሀገራችን ልመና እንደመልካም ባህል በመቆጠሩ አሳፋሪና አሸማቃቂ መሆኑ ከቀረ ቆይቷል:: ሁሉም እጆቹን ዘርግቶ ምፅዋት ጠያቂ ሆኗል ማለት ይቻላል:: «ሰርቼ ነገ ያልፋልኛል» የሚለው ተስፋ በዜጐች ዘንዳ እየተሟጠጠ መጥቷል:: ቅስማችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር

ተሰብራል:: ልዩ መታወቂያችንም ድህነት ሆኗል:: ለዚህ አሳፋሪ የድህነት ቀውስ የተዳረግነው ደግሞ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት ልናገኝ ባለመቻላችን እንደሆነ ብዙዎች በምሬት ይገልፃሉ:: በቀደማዊ ኃ/ሥላሴ ጊዜ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በድርቅ ሳቢያ ተከስቶ የነበረው ርሃብ በደርግና በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን ከተፈጥሮ ድርቅ መስፋፋት ጋር የአስተዳደር ድርቅም እጅግ በመስፋፋቱ ከሥርአቱ ብልሹነት ተዳምሮ በሚሌዮኖች የሚቆጠሩ ዜጐች ባልተቋረጠ መልኩ ለከፋ ርሐብ ተጋልጠው ይገኛሉ:: በዚህ ምክንያትም ምፅዋት ለጋሽ አገራት ተሰላችተዋል::

እንደውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያ ዜጐቿን የምትመግብበት በቂ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት አላት:: በድርቅ በተደጋጋሚ ሁኔታ ብትጠቃም ለራሷ የምትንሰፍ አልነበረችም:: እሷን እየመታት ያለው ድርቅ «የመልካም አስተዳደር እጦት ድርቅ ነው:: » መልካም አስተዳደር ከሌለ ደግሞ ፍትሕ ሊኖር አይችልም:: ፍትሕ ከሌለ እድገት ብሎ ነገር የሚታሰብ አይደለም:: መልካም አስተዳደር እንዳይሰፍን ደግሞ ጋሬጣ የሆነን በደርግ ግዜ እንደ ሸቀጥ ተሶቤት ሕብረት ተቀድቶ የመጣው የኮሚኒዚይም ሥርአት የአገሪቱን ኢኮኖሚ እግር ተወርች ተብትቦ በማሰር አቀጨጨው:: ውስጥ ውስጡንም የግል ብልፅግና ቀስ በቀሰ እያቆጠቆጠ ብዙሃኑ ሕዝብ ግን ምስጥ እንደበላው እንጨት ኑሮው እያደር ነኮተ:: የልመና ባሕልም ፈጠረ::

ደርግ በትጥቅ ትግል ቢወገድም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኮሚኒዝም የማነቆ ሥርዓት አለመላቀቃችን ዛሬ ግሀድ እየሆነ ነው:: እንዲያውም አንዳንዶች እንደሚሉት ኢህአዴግ አፍቃሪ አልባኒያ በመሆኑና የሚመራበት መርህ (አብዮታዊ ዴሞክራሲ) በመሆኑ የችግራችን መጠንና ጥልቀት እጅግ የከፋ እየሆነ መጥቷል::(አብዮት) እና ዴሞክራሲ በምን መልኩ ተጣጥመው (ልማታዊ መንግስት) ሊባል እንደሚችል ግራ የሚያጋባ ነገር ነው:: በሕዝቡ ዘንዳ የሚሰነዘረው ሃሳብ (አብዮታዊ ዲሞክራሲ ብሎ ልማታዊ መንግስት ኢህአዴግ እራሱን ከማሞካሸት ያለፈ ፋይዳ እንደሌለወ በተግባር እያየነው ነው::) ይህንኑ ተከትሎ «ሙስና» ሥር ከመስደዱና ከመስፋፋቱ የተነሳ አሰነዋሪና አሳፋሪ መሆኑ ቀርቶ ሕግ ወጥቶለት ይፋ ባይሆንም የሚያኮራና የሚያስመካ እየሆነ መጥቷል:: ዛሬ የመንግስት ባለሥልጣናት እንደየደረጃቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሙስና ተዘፍቀዋል::

የኢህአዲግ ባለሥልጣናት በሙስና ከመዘፈቃቸው የተነሳ የሕዝቡን የሰቆቃ ኑሮ እና የሃገሪቱን ውድቀት ወደ ጐን በመተው ከሥልጣናቸው በሰላማዊ መንገድ ላለመልቀቅ የ2002 ምርጫን ለማደናቀፍ መግለጫ በመግለጫ በማዥጐድጐድ የቁራ ጩህት ሲጮሁ ይደመጣሉ:: በተለይም አንድነት /መድረክን በከፍተኛ ደረጃ ስለተፎካከራቸው እሱን በመወንጀል እያራመዱት ያለው የሽብር ጩኸት ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል:: በሙስና ያካበቱን ሀብት በሰላም ተቀምጠው የሚበሉበት ሁኔታ አልታየችሁ ስላላቸው የሽብር ሕግ አውጥተው ሽብርተኝነትን እንዋጋለን እያሉ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ላይ የሽብር ቅስቀሳ ማካሄድ ዛሬ ኢህአዲግን ዕርቃኑን ያስቀረ ገሃድ ሆኗል:: «የምንለውን ይቀበላል፤ ሕዝቡ ምንም አያቅም» እየተባለ በየምሽቱ በቴለቪዥንና በሬዲዮ የሚለቀቀው ነጭ ኘሮፓጋንዳ ከማፌሪያነት የዘለለ ምንም ዓይነት ጥቅም እንደማይሰጣቸው የኢሕአዴግ ሙስኞች ሊረዱት ይገባል:: ለመሆኑ «ሙስና » ምንድን ነው? በቅድሚያ ይህንን ጥያቄ መመለስ ይኖረብናል አራት ፍችዎችን የያዘ ነው:: እነሱም:-

1. ሙስና ማሰነ፣ለፋ ከሚለው የግሥ ቃል የወጣ ሲሆን መጣር ፣በሥራ ቆላና ደጋ መውጣትና መውረድን ያመለክታል::

2. ሙስና- ምስና የሚባል ዛፍ አለ ቅርፊቱ ተቀጥቅጦ ፣ ቅጠሉ ተጨቅጭቆ በወሃ ተበጥብጦ ሲጠጡት ኮሶ ያሸራል:: እንደ ኮሶ ፍሬ ማለት ነው::

3. ሙስና ለዛ፣ ውበት፣መልክ ከፀባይ አጣምሮ ወይንም አዋህዶ የሰጣቸው ማለት ነው:: በዚህ ፍችው በአማራው ሕብረተሰብ ጎልቶ ይታወቃል:: እንደ አበባ ረጋፊ፣ ፈራሽ፣ሟች እንደ ማለት ነው:: አንድን የሞተች ሴት ወይንም ሰው «አየ ሙስና፣ እየለዛ፣ አየ ውበት ----- » እያሉ በቅዘመ ስሜት ማድነቅ ይቻላል::

4. ሙስና በዚህ ፍችው የግዕዝ ቃል ሲሆን በአማርኛ « ጥፋት» ማለት ነው:: ታዲያ ዛሬ «ሙስና» ስንል ካራቱ የትኛውን ፍች ይዘን ነው? ሙሰኞቹ ቢጠየቀን ግን ያለጥርጥር በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሰውን እንደሚሉ ገጠመኞች ነን:: ነገር ግን ማለት የተፈለገው በደርግ ጊዜ «ንቅዘት» ይባል የነበረው ዛሬ ሙስና የተባለ ይመደባል:: ንቅዘት «ነቀዝ» ከተባለው በልቶ ከማይጠረቃው የሰብል ፀር ከሆነው ተባይ የተገኘ ሲሆን ፅንሰ ሐሳቡን ለመጨበጥ ማንም አይቸገርም:: ነቀዘ ያገርን ኢኮኖሚ ዱቄት ያደርጋል:: ሙስና ለዚህ ዘመን ነቀዞች ተስማሚ ፍች ነው:: በተለይም የመጨረሻው ፍች «ጥፋት »የሚል በመሆኑ ሙሰኞች ያላንዳች ጥርጥር የአገርን ኢኮኖሚ ያጠፋሉ:: ሙሰኞች የአገርን ኢኮኖሚ ብቻ በማጥፋት አይወሰኑም:: ጥፋታቸው ሁለገብ ነው:: የአስተዳደርን ሥርአት ያቀውሣሉ፤ የፍርድ ሂደትን ያዘባሉ፤ ፍትሕን ያጠፋሉ፤ የዴሞክራሲን ጭላጭል ከነጭራሹ ያዳፍናሉ:: ግለሰቦችን እጥንታቸው እስከሚቀር ድረስ ይመጣሉ፤ የካዝና ገንዘብ ይመዘብራሉ፤ ሴራን በሕዝቦች መሀከል በማሠራጨት ይከፋፍላሉ፤ ሠላም ይነሳሉ:: ያናክሳሉ የተረጋጋውን ማሕበረሰብ በማበጣበጥ የጎሪጥ ያስተያያሉ፤ በዚህ ሁሉ ቀዳዳ እየተጠቀሙ የነሱን ኑሮ ያመቻቻሉ:: ዛሬ በሀገራችን ሰፍኖ የሚታየው ችግር የተጠቀሰው ነው:: ይህንን ኢሕአዴግም አይክድም:: እያድበሰበሰ ያለው ግን ሙስናን በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ማስታወቂያ አጠፋለሁ በማለት ሲሳለቅ ይታያል::

በመሠረቱ ሙስናና ሙሰኞችን በጀርባ አዝሎ ልማት አካሄዳለሁ ማለት የሚታሰብ አይደለም:: « በአብዮታዊ ዴሞክራሲ » መርህ እየተመሩ «ልማታዊ መንግስት ነኝ » ማለት ቀልድ ነው:: ስለአብዮታዊ ዴሞክራሲነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ ጊዜ ደህና አድርጎ ያውቀዋል:: የኢሕአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግፋ ቢል ካልባኒያ ቢቀዳ እንጂ አዲስ ካባ ልብሶ ከጨረቃ አልመጣም:: ስለዚህ ሕዝባችን ሣይዘናጋ በ2002 ምርጫ ሙስናንና ሙስተኞችን በካርዱ ጠራርጎ ከሥልጣናቸው ማውረድ አለበት:: ይህ እስካልሆነ ድረስ ግን አገራችን ከልመናና ከበፀዋትም አትላቀቅም:: ሁላችንም የድርሻችንን ለመውጣት ቁርጠን እንነሳ:: ሰላማዊ ትግል ምንግዜም ያሸንፋል!!

## ተናገር ይውጣልህ

ከ ኢ.መ

አየሁህ ወንድሜ መተንፈስ አቅቶህ
እንደ ወራ ቅጠል በቁምህ ጠውልገህ
ሥጋቱ ጭንቀቱ እንቅልፍ አሣጥቶህ እንደ
ዱር ሚዳቋ አሥር አሥር ጊዜ ትበ ረግጋለህ!

ተናገር ይውጣልህ
አንድ ቃል ሳይወጣህ ለምን ትሞታለህ?
ባያድልህ እንጂ አንተም ባላገር ነህ!
እነሱ አፈናቅለው ተፈናቃይ ሲሉህ
መብትክን ስጠይቅ ሽብርተኛ ሲሉህ
ቀን በእህህታ ሌሊት ትቃዣለህ
ሣትኖር እየኖርክ አለሁኝ ትላለህ
አንተ ሣያልፍልህ ለሰው ትለፋለህ
ነገ ለልጆችህ ፍዳ ታወርሣለህ
ይህን ሣትናገር ለምን ትሞታለህ
ባያድልህ እንጂ አንተም ባላገርነህ::
በገዛ አገርህ ባይታወር ሆነህ
አንገትህን ደፍተህ እህህ ትላለህ
እነሱ ሲበሉ አንተ ጦም ታድራለህ
እስከመቾ ድርስ በቁም ትሞታለህ?
አንተምኮ ሰው ነህ ሰው ትፈልጋለህ!
ተናገር ይውጣልህ
ለምን ዝም ትላለህ?
«ዝምታ ወርቅ ነው» ብለው ቢደልሉህ
ፍፁም አትስማቸው፤ ተናገር ይውጣልህ!
ነፃነትክን አውጅ በካርድህ ተጠቀም
ነገ ያገር ተስፋ ትሆናለህ አንተም!!

## ታሪክ ራሱን . . .

*(ከገፅ 3 የዞረ)*

ዘይቤዎች ሆኖዋል:: በዚህ ብቻ ሳያበቃ የምርጫ ካርድ ቤት ለቤት እየተዞረ እስከመስጠት ተደርሷል:: ተቃዋሚ የተባሉ የመንግሥት ሠራተኞች የዓመት ፍቃድ ይከለከላሉ ፣ ለፖርላማ ዕጩ አድርገን ያቀረብናቸውና አባላቶቻችን በአንድ ቦታ መግተው እንዳይቀመጡ በስራ ዝውውር ምክንያት ባዛኝ እንዲሆኑ ይደረጋል::

አስጊ ሁኔታ ላይ መገኘታችን ለማንም ግልፅ ነው:: በአጠቃላይ አባላቶቻችን የሲቢል መብቶቻቸውን ማጣታቸውን ያደባባይ ሚስጥር ነው:: የዕጩ ቤተሰቦችን ማስፈራራት ቢሮዎቻቸውን መስበር እየተደጋገመ ሲፈፀም ታይቷል:: እኛ አንበረከክም አልን እንጂ ከምርጫ ተስፋ ቆርጠን እንድንወጣ ያልተፈነቀለ ድንጋይ ያልተቆረጠ ቅጠል የለም:: የሕዝብ አንጡራ ገንዘብ በሆኑ መገናኛ ብዙሃን በተሰጠን አጭርና እዚህ ግባ የማይባል የቅስቀሳ ሰዓት ተጠቅመን ከሕዝባችን ጋር እንዳንገናኝ ዕቀባው መልኩን እየቀያየረ ተፈፃሚ ሲሆን ሰነባብቷል:: በዚህ ሁኔታ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሆነን የምርጫ ዘመቻችንን ማካሄድ መቻላችን የሚታሰብ ሆኖ አላገኘነውም:: የከሌና የከሌ ወኪል ናችሁ ከመባል ባሻገር እንደ ዜጋ ተቆጥረን እንደ ድርጅት ታይተን ነፃ አስተሳስብን ማራመዳችን መቻላችን ዘበት እየሆነ ነው::

መድረክ እነዚህ ያልተገደቡ ስድቦች ፣ ማስፈራሪያዎችና ዛቻዎች ማስጠንቀቂያዎች ህገመንግሥታዊ ባለመሆናቸው እና የሥነ ምግባር ደንቡን ስለሚፃረሩ በአስቸኳይ እንዲቆሙለት እየጠየቀ በሬድዮና በቴሌቪዥን ዝግጅቶቹ በሲንሰርሽኘ ዓይነተ የሚደርስበት ዕቀባ ይገታ ዘንድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ይህንን መግለጫ ለመስጠት ተገዷል

**መድረክ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያሸንፋል! !**

# ካስተዋልነው

# «በፖለቲካ አቋም ምክንያት ብርቱካን ላይ የተቆለፈው የነፃነት በር ሊከፈት ይገባል!!»

## አቶ ስየ አብርሃ

- ከትግሉ ዓላማዎች አንዱ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ የነበረ ቢሆንም በትግሉ ወቅት የነበረን ዓላማ ደርግን ጥሎ ስልጣን መቆጣጠር ብቻ አልነበረም፤
- ዜጎች ያለ ሥጋት በሙሉ ነፃነት ተገቢውን ሰብዓዊ ክብር እንዲጎናጸፉ ማድረግ የትግሉ አላማ ነበር፤
- የህዝቦቿ እኩልነት የተረጋገጠበትና ሉዓላዊነቷ የተ ጠበቀ አገር ለትውልድ ማውረስም የትግሉ ዓላማ ነበር፤
- እውነትና ፍትሕ የሚከበርበት ስርዓት ለመዘርጋት የተ ደረገ ትግልም ነበር፤
- ድህነትና የምግብ ርዳታ ቀርቶ ራሳችንን ችለን ሰፊ ልማትን ለማምጣት የሚያስችለንን ስርዓት መዘርጋትም የትግሉ አላማ ነበር፤

ከኤርትራ ጋር የሚኖረንን ዝምድና በሚመለከትም ችግሩ ተፈትቶ ቢያንስ ሰላምን እግኝተን መኖር ምኞታችን ነበር::

እነዚህ ፍላጐቶችና ዓላማዎች በትግሉ ወቅት ይዘናቸው የነበሩ ቢሆንም አንዳንድ እንከኖችንና ችግሮችንም ጭምር የያዙ እንደነበሩ አይካድም:: ሆኖም በሂደት እየተማሩ በማስተካከልና ሂደቱን ለማቃናት የሚያስችል ሰፊ ዕድል ነበር:: በዚያ መሰረት የተተገበሩ የማስተካከያ ርምጃዎች እንደነበሩም ይታወቃል::

የኢትዮጵያ ህዝብ ጉድለቶችን እየተመለከተም ቢሆን የርምት ርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችል ትዕግስት አሳይቷል፤ እድልም ሰጥቷል:: ሆኖም ሕወሓት ትዕግስቱን በማክበር በዕድሉ ለመጠቀም ባለመቻሉ የታለመው አልተገኘም፤ ማሻሻልና ማረሙ ቀርቶ የነበሩ ጥቂት አዎንታዊ ጅምሮችም ተቋርጠው ቀርተዋል::

የኤርትራን ችግር ለመፍታት ሕወሓት ከጅምሩ የተከተለው መንገድ ከችግር ያልፀዳ እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ተፈጥሮልን የነበረው ችግሩን ለማረም የሚያስችል አጋጣሚ ሊያመልጠን በመቻሉም ወደባሰ ማጥ ተ ዘፍቀናል:: አገራችን ወደብ አልባ ሆና መቅረቷ ሳያንስ እንደገና ወደ ጦርነት ለመግባት ተገደናል:: ጦርነቱ ካልቀ ረልንም አንደኛችንን ጉዳያችንን ጨርሰን መውጣት ስንችል አሁንም መቋጫ ወደሌለው ችግር ውስጥ ገብተናል:: ሰራዊታችን አላረፈም:: አሁንም ምሽግ ውስጥ ነው:: የትግራይም ክልል በኢትዮጵያ ውስጥ ለኢንቨስትመንት ከማይመረጡ ያልተረጋጉ አካባቢዎች አንዱ ሆኖ ይገኛል:: ባለፉት አሥራ ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ ትግራይ ውስጥ በፋብሪካዎች ፋንታ የጦር ሰፈሮች ቁጥር መጨመሩም የችግራችንን ክብደት ያመለክታል::

እጅግ የሚያሳዝነው እውነታም ያ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ብዙ ዋጋ የከፈለው ህዝብ የጥቃት ዓላማ እንዲሆን መደረጉ ነው:: ለፍትሕና ለዴሞክራሲ የሚደ ረግን ትግል ከሻዕቢያ ጋር በማስተሳሰር ለማጥላላት የሚያደረገው ፓለቲካዊ ጥረትም የዚህ አንዱ አብነት ነው::የሻዕቢያ ወረራ ዱብ እዳ ነበር::

ሆኖም ለጉዳዩ የማያዳግም መቋጫ ለማድረግ የሚያስችል ዕድል ፈጥሮልን ነበር:: በዚህ ጉዳይ ላይ ከ 1991 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጠረው ልዩነት ነሐሴ 1991 ዓ.ም በተካሄደው የማ/ኮ ስብሰባ የተፈጠረውን ልዩነት በውይይት ለማስተካከል ተወስኖ የነበረ ቢሆንም በጦርነት መሃል ይህንን ችግር ለመፍታት እንቀመጥ ዘንድ ሁኔታዎች አይፈቅዱም በማለት ነገሩን አቆይተን ስናበቃ ጦርነቱ መቋጫ ከተበጀለት በኋላ 1993 ዓ.ም ስብሰባ ተቀምጠን ነበር:: የልዩነታችን መንስኤ ሉአላዊነትና የአገር ጉዳይ ሆኖ ሳለ በውይይቱ ሂደት የሙስናና የዴሞክራሲ አጀንዳን በመሰንቀር የትኩረት አቅጣጫን የማስቀየር ዘዴ ተቀይሶ ነበር:: ሙስና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚል እውነተኛ አቋም ካላችሁ እንግዲህ የሁላችንም /ንብረት/ ይዞታ እንዲፈተሽ ሀሳብ አቀረብን:: ይሄኔ ሃሳቡ የጸረ - ሙስናውን ትግል ለማደናቀፍ የተሰነዘረ ነው አሉን::

ልዩነቱን ይፈታል ተብሎ የተጠራው የማ/ኮ ስብሰባ ችግር ውስጥ ሲገባም ጉባኤ የጠራና አቋማችንን ይዘን እንቅረብ ማለታችን ወንጀል ሆኖ ጉባኤ እስኪጣራ ድረስ ከኃላፊነታችሁ ታግዳችኋል የሚል ቀላጤ ደረሰን:: በዚያውም ከድርጅቱና ከመንግስት ኃላፊነታችሁ ታግዳችኋል የሚል ቀላጤ ደረሰን:: በዚያውም ከድርጅቱና ከመንግስት ኃላፊነት አስወጡን:: አንዳንዶቻችን ደግሞ ከመላው ቤተሰባችን ጋር ወህኒ አወረዱን:: ራሳችንን ለመከላከል በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ አስቀምጠውን ሲያበቁ ስማችንን ለማጥፋት ለበርካታ አመታት ሕወሓት በአንድ በኩል ለህገ መንግስቱ ተገዢ መሆኑንና በዚያም እንደሚመራ፤በሌላ በኩል የአብዮታዊ ዴሞክራሲን እንደሚከተልና በዚያም እንደሚመራ ይገለፃል:: ታዲያ የአብዮታዊ ዴሞክራሲን መርህ በህገ መንግስቱ ሰፍረው ከሚገኙ መርሆች ጋር የሚጋጭ ነው::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ በተፈጥሮው የመድብለ ፓርቲ ፅንሰ ሃሳብን አይቀበልም:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድን የፓለቲካ መስመር አንድ ፓርቲ ሁሉን ሊመራና ሊቆጣጠር ይገባዋል የሚል አስተሳሰብን ያራምዳል:: ከዚህም በመነሳት የፓለቲካ ፓርቲዎች ህልውናና አቋሞቻቸው፣ የሕ/ሰቡ ነፃ ድርጅት ድምፆች ህልውና ሁሉንም ዜጐች በእኩልነት ዓይን የሚመለከቱና የሚያገለግሉ መንግስታዊ ተቋሞችን ህልውና አይቀበልም:: ሁሉም በመሪ ፓርቲውና በአቋሞቹ ቁጥጥር ስር መዋል አለባቸው የሚል ነው:: ይህም በህገ መንግስቱ ውስጥ ከሰፈሩት መርሆች ጋር በቀጥታ የሚጋጭ አቋም ነው::

ሕወሓት መሪዎች የምናቀርብላቸው መልዕክት አንድና ግልጽ ነው፤ የናንተማ ፍርድ ከዛሬ ስምንት ዓመት ጀምረን አውቀነዋል፤ ታስረን ተገርፈንበትም በፅናት ተቋቁመን በመቆም እዚህ ደርሰናል /ለዚህ በቅተናል/:: አሁን ደግሞ በተራው ሕዝብ ፍርዱን እንዲሰጥ ሁኔታዎችን አመቻቹለት፤ ፍርዱ የህዝብ መሆኑን ተቀበሉ እንላቸዋለን:: በአንድ እጅ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሌላኛው ህገመንግስቱን ይዛችሁ ሳይሆን በህገ መንግስቱ እንደተደነገገው ከፍርሀትና አድልዎ ነፃ ለሆነ ምርጫ ቁሙ ነው የምንለው::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰፊ አድማስ የሚሸፍን ሁለንተናዊ ልማትን አይቀበልም:: «ርሻ መር የኢንዱስትሪ ልማት » እከተላለሁ በሚል ኢንዱስትሪን ጨምሮ ሌሎቹን /የኢኮኖሚ/ ዘርፎች አምክኗቸው ይገኛል:: ርሻውም ቢሆን ኢንዱስትሪውን ሊመራ ቀርቶ ራሱንም ካለበት ሊያንቀሳቀስ አልቻለም:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሌሎቹን /የኢኮኖሚ/ ዘርፎች ጨምድዶ መያዙ ሳይበቃው ባለሃብቱንም ጭምር ጨምድዶ በመያዝ አሽከር ሊሆንለት የሚችል ባለሃብት ለመፍጠር በጥረት ላይ ነው:: «ኪራይ ሰብሳቢ እና ልማታዊ» በማለት ባለሃብቱን መለያየት የተፈለገበት ምክንያት ይኸው ነው:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንዱን ፓርቲ ብቸኛ ገዢ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ፓርቲው ራሱ ባለሃብት እንዲሆን በማድረግ ግለሰብ ባለሃብቱን ለማክሰም የሚያልም መስመር ነው:: በገበሬው ላይ ገዢ ዘመናዊ ጉልተኛነት አበዳሪ በመሆን ሁሌም ጥገኛው በማድረግ የሚያኖር የፓለቲካ መስመር ነው::

ይህ አካሄድ በልማት ወደፊት ሊያራምድ ቀርቶ የነበረውን ሂደት እስከማጨናገፍ ደርሷል:: የትግራይንም /የልማት/ ሁኔታ ብንመለከት ተሃድሶ ከተባለው ተረት ተረት ወዲህ የተሰራውን ከዚያ በፊት ከተሰራው ጋር ብናነፃፀር ሰማይና መሬት ነው:: ድሮ ከነበረው ርምጃ ጋር በሚጠጋ መጠን ሊጨምር ቀርቶ በዚያን ጊዜ በጋራ የታቀደውንና የተጀመረውን የሚያጨናግፍ ስራ ነው የተሰራው:: በመስኖ



ላይ የተሰራው በምግብ ራስን የማስቻል ዕቅድ ለመተግበር የተባለ ድርጅት ተቋቁሞ የራያን መስክ ለማልማት ትልቅ ሥራ ተጀምሮ ነበር:: ይህም «ሳርት» ለድሃው ገበሬ የሚጠቅምና ገበሬውን ማዕከል ያደረገ ዕቅድ ነበር::

በርካታ ምሁራንና ባለሙያዎች የተሳተፉበት ገበሬውን በምግብ እህል ራሱን ያስችሉታል የተባሉ ትላልቅ ዕቅዶች ነበሩ:: እነዚህም ተጨናግፈው እንዲቀሩ ከተደረጉት ዕቅዶች የሚጠቀሱ ናቸው::በእነዚህ ፈንታ ተሐድሶ ለገበሬው ያቀረበለት አማራጭ ትንሽ ስራ ሰርቶ ላዩ ላይ ላስቲክ ማንጠፍና ውሃ ማቆር ነው::

የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ ሊያስተሳስር የሚችል ፓሊሲ ለማምጣት አልቻሉም:: የቆየውን ቁስል እያከሙ ሰው በአንድነት እንዲተቃቀፍና እንዲቀራረብ በማድረግ ፈንታ የቆየው ቁስል እያጋነኑና ልዩነቶችን እያራገቡ ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በእርስ በጥርጣሬ ዓይን እንዲተያዩ ሲያደርግ ቆይቷል:: ህዝቡ በአንድነት ሲነሳባቸው ደግሞ ትግራዋዩን ሕወሓት ፣ ኦሮሞውን በኦህዴድ ወዘተ በመግባት ስሜቶቹንም እየቆሰቆሱ ሲለያዩት ቆይተዋል:: በዚህም አማካይነትኢትዮጵያውያን የጋራ ጉዳዮቻቸውን በአንድነት ለማየት የማይችሉበትን ሁኔታ ተፈጥሯል:: በትግራዩ እየታየ ያለው በጥርጣሬ ዓይን የመታየት አዝማምያ ኦሮሞውን፣ አማራውን፣ ሶማሌውን ፣ ሲዳማውን፣ ጋማቤላውን እና ሌሎች የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ላይ እያጋጠመ ያለ ችግር ነው:: የሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያውያን መካከል በአንድነት ፋንታ ከመጠን ያለፈ ጥርጣሬና የአንድነታችንን መዳከም ፈጥሮ ይገኛል::

ለችግሩ መፈጠር አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የራሳቸው ድርሻ እንደነበራቸው ይታወቃል:: እንደምሳሌ ለማውሳትም ያክል በምርጫ 97 ትግራዋይን ከሕወሓት ለይቶ የማያይ ቅስቀሳ ነበር:: አገራዊ ቁም ነገሮችንና ወንድማማችነትን በማስተማር ፈንታ ትግራዋዩን የፓለቲካቸው መለማመጃ ያደረጉ ፖለቲከኞች ታይተው ነበር:: ይሁንና በዋነኛነት ይህን የመሰለውን የጥላቻ ነቀርሳ የፈጠረው የገዢው ፓርቲ ፖለቲካ መሆኑ ከቶ መዘንጋት የለበትም:: ገዢው ፓርቲ የሕወሓት /ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህና የብሄር ፖለቲካ ማዕከል ያደረገው ፖለቲካው መሆኑ ከቶ ሊዘነጋ አይገባውም::

የሕወሓት መሪዎች የራሳቸውን ችግሮች እንደመመልከት ችግሩን በተቃዋሚዎች ላይ ይለጥፉታል:: ይህንንም እምነታቸውን በትግራይ ህዝብ አዕምሮ ውስጥ ለማስረፅ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ይታወቃል:: ስህተቶቹ ቢመዘኑ በስልጣን ላይ ያሉት የሕወሓትና የጓዶቹ ድርሻ የበለጠ እንደሚሆን መገንዘብ ይገባል:: እነሱ ለፍትህ፣ ለፍቅርና ለአንድነት ተግተው ቢሰሩ ኖሮ ችግሩ እንዲህ ባልገዘፈ ነበር::

(ወደ ገፅ 7 ዞሯል)

# ሰዎች ምን ይላሉ?

## ይድረስ ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች

ከእያሱ በዕደማርያም

ከሰሞኑ የንብረተሰቡ የመነጋገሪያ ርዕሶች መሀከል አንዱ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና የሌሎች ተቋማት ተማሪዎች በየካምፓሳቸው በሚቋቋሙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ይመርጣሉ ስለተባለ በየተቋማቱ ምዝገባው እየተጧጧፈ በመሆኑ ወሬው በስፋት እየተነገ ነው፡፡ ወሬው በዚህ ብቻ ሳያበቃ የተማሪዎቹ የምርጫ ወረቀቶች ወደ መጡባቸው የአገሪቱ የምርጫ ወረዳዎችና የምርጫ ጣቢያዎች በመላክ እዚያ እንደ ደረሱ ይቆጠራሉ እየተባሉም በመናገር ላይ ነው፡፡

በመንግስት በኩል ወይንም በምርጫ ቦርድ ተማሪ ዎች በሚቋቋሙት ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች እንደማንኛውም ዜጋ ምርጫ ያካሂድ እንደሆነ የተነገረ ነገር የለም፡፡ መጋቢት 28 ቀን በመንግስት የብዙሐን መገናኛዎች እንደተገለፀው ከሆነ 150 ሺህ ታዛቢዎች መዘጋጀታቸውን ቢገለፅም በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች መገኘትና አለመገኘት አልተገለፀም፡፡ ተ ቃዋሚ ፓርቲዎችም ተካፋይ ስለመሆናቸው የተገለፀ ነገር የለም፡፡ ጉዳዩ በእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ መሻት ብቻ ሳይሆን ያውም መልስ ሰጭ ከተገኘ የሚፈታ አይመስልም፡፡ ተ ማሪዎች ድብዓቸውን ከሰጡ በኋላ ወደ መጡበት ወረዳዎችና ቀበሌዎች የድምፅ ወረቀቶቻቸው የሚላኩት በምን ዓይነት መንገድ እንደ ሆነ በሕዝብና በተ ፎካካሪ ፓርቲዎች በግልፅ መናገር አለበት፡፡ የድብብቆሽ ጨዋታ መሆን የለበትም፡፡በሌላ በኩልም ከልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የሚላኩት የተማሪዎች ድምፆች ሲለኩ ታዛቢዎች እንዴት ሊታዘቡ እንደሚችሉ እስካሁን ግልፅ አልሆነም፡፡

ይህም ከዚህ መንግስት ባህሪ አንፃር ሲታይ በጣም አሳሳቢ ነው፡፡የዚህ ተመሳሳይ የሆነ ሌላም አቢይ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የዲያስፖራው የመምረጥ መብት ጉዳይ ነው፡፡ አለመታደል ሆኖ እንጂ «ዴሞክራሴን አሰፈንናል፣ የዜጐችን መብት አክብረናል» የሚሉ ዜጐቻቸው በኤምባሲዎቻቸው ተገኝተው የሰጡትን ድምፅ በዲኘሎማቲኮቻቸው ወይንም በፖስታ በኩል ባስቸኳይ ወደ አገር ቤት ተልኮ በሥርዓት ቆጠራው ይከናወናል፡፡ ወደኛ አገር ስንመለስ ግን ሁኔታው የተገላቢጦሽ ነው፡፡ ውጭ የሚኖረው ዲያስፓራ አብዛኛው የተቀዋሚ ዎች ደጋፊ ነው ስለሚባል ገዥው ፓርቲ ውጭ በሚኖሩበት ዜጐች መብት ይሰጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ገዥው ፓርቲ ተነሳሽነት ይኑረውም አይኑረውም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህንን በተመለከተም ትኩረት ሰጥተው ውጭ የሚኖሩትን እናትና አባቶቻችን፣ እህት ወንድሞቻቸውን ባለመርሳት የዜግነት መብታቸው እንዲከበርላቸውና የፈለጉትን የመምረጥ ዕድል እንዲረጋገጥላቸው ልትሟገቱላቸው ይገባል፡፡

ይህንን በማስፈፀምም በቂ ነው ባይባልም ጊዜ አለ፡፡ ጥያቄዎቻችን ገዥው ፓርቲ እንደማይመልሳቸው እናውቃለን፡፡ ይሁን እንጂ እናንተ ጠይቁ፡፡ መጠየቃችሁና መልስ ማጣታችሁ በራሱ ታሪክ ሆኖ ይቆጠራል፡፡ የተማሪዎች ድምፅም መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል በጥንቃቄ ተከታተሉ በተረፈ በርቱ ተበራቱ ሕዝብ ከጎናችሁ ነው!!

## በፖለቲካ አቋም. . .

### (ከገፅ 6 የዞረ)

ሕወሓት ተሰኝተን ትግል ስንጀምር እናርመዋለን ብለን የተነሳንለት የዚህች አገር ችግር እንደፍጐታችንና እንደተመኘነው አልፈታነውም፡፡ አሁንም ችግሩ ውስጥ እንገኛለን፡፡ የድሮው ስጋታችን መልኩን ከመቀየሩ በቀር አልፎፋም፡፡ ህዝባችን በተለይም ትግራዋይ ፍትህ ማጣቱና ከድህነቱ የሚወጣበት መንገድ የሚታየው አለመሆኑ በተጨባጭ የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ሆኖም ይህን ለመለወጥ በሚደረግ ትግል ውሰጥ በትጋት ያለመሳተፍ አዝማሚያ ይታያል፡፡ በመሃል አገር የሚታዩትን የፍትህና የለውጥ ፍላጐቶች በተስፋ ሳይሆን በስጋትና በጥርጣሬ ሲመለከት ይታያል፡፡

ኤርትራን በሚመለከት ሲከተለው የቆየውን እስከአሁን ሰላምን ያላመጣውን ፖሊስ በጤነኛ መንፈስ ገምግሞ በማቃናት ፈንታ የኢትዮጵያ ባሕር በር የማግኘት ተፈጥሮአዊ፣ታሪካዊና ህጋዊ መብት አላት የሚሉትን ወገኖች በአንድ በኩል እንደዘረኞች ሲያቀርብ በሌላ በኩል... «የሻቢያ ሽርኮች» ናቸው በማለት አስነዋሪ ጥላሸት ይቀባቸዋል፡፡ በዚህ ክስ ውስጥ የሕወሓትና የኢህአዴግ መሪዎች የነበረውንም ጭምር በጣም ያስገርማል፡፡

- እንዲህ አይነት አካሄድ በጸብና ስጋት ውሰጥ በቀጣይነት የሚኖር እንጂ ከዚያ የማያስወጣ አይደለም፡፡ መፍትሄ በችልታ መንገድ በመቀጠል ሳይሆን ቆም ብሎ ነገሮችን እንዳዲስ መመልከት ነው፡፡
- እኛ ያልነው መንገድ የእኛ አካሄድ ካልሆነ በቀር ሌላው መንገድ ሁሉ የጥፋት መንገድ ነው የሚለውን ሕወሓት ለረጅም ግዜ ይዞት የቆየው አካሄድና አስተሳሰብ የትም እንደማያደርሰው /አንደማይሰራ/ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
- የሀገር ጉዳይ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጉዳይ መሆኑን እንዲገነዘቡና ሀገራዊ አጀንዳዎች ሕወሓትና ጓዶቹ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ፖለቲከኞችን የሚመለከቱና የሚያሳስቡ ጉዳዮች መሆናቸውን በመቀበል ከሁሉም ጋር ተባብሮ በመሄድ መግባባትን በመፍጠሩ ብቻ የዚህን ሀገር ችግር ለመፍታት እንደሚቻል ሊታመንበት ይገባል፡፡
- ይህንን አለመቀበል በዚህ ችግር እኛ መድከማችን ሳያንሰን ቀጣዩ ትውልድ ችግሩን እንዲወርሰው ማድረግ ነው፡፡ መድረክን ያቋቋምንበት ምክንያት ይህንን የተከማቸ ችግር በጋራ ሆነን መፍትሄ ለመፈልግና ችግር መቋጫ በማበጀት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕወሓትና ጓዶች መሪዎች «መድረክ የኢትዮጵያን ውስብስብ ችግሮች የሚፈታበት ብቃት የለውም» በማለት ቢመጻደቁም እኛ ይህንን አዲስ አካሄድ እንዲመጣ ምክንያት የሆነን ሕወሓትና ጓዶቹ ከ 18 ዓመታት በኋላም ቢሆን ፈተናውን ለማለፍ አለመቻላቸውን በመገንዘባችን ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር ህዝቦችን አሁን ባለው የሕወሓትና/ኢህአዴግ አገዛዝ ስር መቆየት አይፈልግም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የለውጥ መለኪያው ሚዛኑ ያለፈው ስርዓት ወይም የአንድ አከባቢ ሁኔታ ባለመሆኑ ኢሳያስ ወይም መንግሥቱ ማነፃፀርያ ሊሆኑት አይችሉም፡፡ ከእነዚህ እሻላለሁ እያለ የሚፎክር መንግስት አይፈልግም፡፡ አሁን የሚፈልገው መንግስት የዓለም ማሕበረሰብ ተቀብሎ የሚመራባቸውንና አብዛኞቹ በአገራችን ሕገ መንግስት ሰፍረው የሚገኙትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ሃገር የሚመራ መንግስት ነው፡፡ በመድረክ ታቅፈን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን መሰባሰቢያችን ሀገር ወደ ተሻለውና በዓለም ማሕበረሰብ ተቀባይነት ባገኘው አቅጣጫ እንድትገሰግስ የማድረግ አላማ ነው፡፡

ሕወሓት ይህን ለውጥ በስጋት ዓይን የሚመለከተው በመሆኑ የትግራይ ሕዝብን በስጋት እንዲመለከተው ለማድረግ ተግቶ እየሰራ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ስማችንን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ አመራሩ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት የትግራይን ሕዝብ አስፈራርተው ሁሌም የእነርሱ መፈንጫ ማድረግ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ከእኛ በላይ ለትግራይ ሕዝብ ስለሚያስቡለት አይደለም፡፡ በየትኛውም መመዘኛ እነርሱ ከእኛ በላይ ሊያስቡለት እንደማይችሉ ታሪካችንና ስራችን ምስክር ነው፡፡

እኛ ይዘነው ያለነው መንገድ የፍቅር የአንድነት የእርቅና ተስማምቶ የመኖር መንገድ ነው፡፡ ከዚህ መንገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ትግራይም ጭምር፡፡ የህሕወሓት አባላትም ቢሆኑ የሚጠቅማቸው ይኸው መንገድ እንጂ ያረጀው የፀብና የእልህ መንገድ አይደለም፡፡ የትግራይ ተወላጆች የሆነው በዚህ መንገድ ብንሄድ ስማችን በክፉ ሳይነሳ ተከብረን በሰላም የምንኖርበት ሃገር ለልጆቻችን እናወርሳለን፡፡

በህሕወሓት /ኢህአዴግ/ ሰፈር ተቃዋሚዎች ስልጣን ከያዙ የሃገር የመከላከያንና ሌሎች ተቋማት እንዲሁም የሲቭል ሰርቪሱን ያፈርሱታል ሰራተኛውንም ያፈናቅሉታል እየተባለ ይወራል፡፡ መከላከያ ሃይላችንም ሆነ ሁሉም ተቋሞቻችን ከአንድ ፓርቲ የስልጣን ዘመን ባሻገር አገራዊ ፋይዳ እንዳላቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ፓርቲዎች በተቀያየሩ ቁጥር የሚቀያየሩ መሆን አይገባቸውም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተቋማት ከፓለቲካ ተጽእኖ ተላቀው ነፃ ተቋማት እንዲሆኑ፣ብሄራዊ ተዋፅኦቸውን በጠበቀ መልኩ ይበልጥ እንዲጠናከሩ መድረክ አበክሮ ይሰራል፡፡ መሠረታዊ እምነቱም ይህ ነው፡፡ ይህን እምነቱን ለማረጋገጥ የተቋማቱን ህልውና ቀጣይነትና ተአማኒነታቸውን ለማጐልበት ማስተካከያዎችን ያደርጋል፡፡ መድረክ የጎበጡና የተበላሹ ነገሮችን ለማስተካከል የሚሰራ እንጂ ተቋማቱን የማፍረስ ይሁን የማናጋት ተልእኮም ፖሊስም የለውም፡፡

በመጨረሻም እኔ ነፃነቴን አግኝቼ ከፊታችሁ ለመቆም በበቃሁበት በዚህ ወቅት የዛሬ 9 ዓመት እውነቱንና የህግን መርሆች በመከተል ፍትህ የበየነችልኝ ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ነፃነቷ ተገፎ ወህኒ ቤት ትገኛለች፡፡ በፖለቲካ አቋም ምክንያት ብርቱካን ላይ የተቆለፈው ነፃነት በር ሊከፈት ይገባል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ብርቱካን ትፈታ ብለን በጋራ እንድንጠይቅ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ብርቱካን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የፓርቲ ሊቀመንበር ለመሆን የበቃች የመጀመሪያዋ ሴት ፖለቲከኛ ነች፡፡ ለሴቶች መብት መቆም ማለት እንደ ብርቱካን ና አረጋሽ የመሳሰሉት ጭምር ወደ ፓለቲካ መድረክ ለሚመጡ ሴቶች ድጋፍ መስጠት ማለትም ነው፡፡ በመሆኑም ለፍትሕና ለመብቶች መከበር የምንታገል ዜጐች ሁሉ በተለይም ደግሞ ሴቶች ለብርቱካን ነፃነት በአንድነት መቆም ይገባቸዋል፡፡

በመካከላችን የብሄር ወይም የፖለቲካ ልዩነት ሊኖር ቢችልም ሁላችንም ሰዎች ነን፣ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ ኢትዮጵያዊነታችን የሁላችንም እጣ ፈንታ የተሳሰረ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ አቋሙ ምንም ይሁን፤ ብሄሩ ምንም ይሁን፤ ምን በማንም ኢትዮጵያዊ ላይ የሚፈፀም በደል በእያንዳንዳችን ላይ እንደተፈፀመ ቆጥረን ግፍና በደልን በተገኘበት ሁሉ ልንታገለው ይገባል፡፡

በተለይም እኛ የትግራይ ተወላጆች ሕወሓት /ኢህአዴግ የሚፈፅማቸውን በደሎች በሚመለከት የራሳችን ነፃ፣ ፍትህንና ፍትሃዊነትን መሰረት ያደረገ አመለካከትና አቋም ያለን መሆኑን ለኢትዮጵውያን ወገኖቻችንና ለአለም ማኀበረሰብ መግለፅ እንደሚያስፈልግ ልንገነዘብ ይገባናል፡፡

አደራቸውን ትከሻችን ላይ አኑረው ለሄዱትና የኃይል አገዛዝን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ ሲባል ለወደቁት የአገራችን ሰማዕታት በሙሉ ዘለአለማዊ ክብር ይገባቸዋል፡፡


**መድረክን ይምረጡ!!**



# መድረክን ይምረጡ!!

## «በመድረክ መጠናከር ኢህአዴግ ብርክ ይዞታል»

### አቶ አንዱአለም አራጌ

አቶ አንዱአለም አራጌ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ጸሐፊ ሲሆኑ አንድነት ካሉት ጠንካራ ወጣት ታጋይ ፓለቲከኞች አንዱ ናቸው:: ምንም እንኳን ስራ ቢበዛቸውም ከፅናት ጋዜጣ ለአቀ ረብንላቸው 4 ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል::

***ፅናት:-*** *ከምርጫ ወሬ እንጀምር መድረክ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ክልሎች በርካታ ስብሰባ ዎች አካሂዷል ከሕዝብም ጋር ተ መካክሯል:: ውጤቱ እንዴት ነው?*

**አቶ አንዱአለም:-** በአጠቃላይ ከ97 በኋላ በተለይ ከቅንጅት መከፋፈል በኋላ የአዲስ አበባ ሕዝብ ተስፋ ቆርጦ እቤቱ ተቀምጦ ነበር:: ወይንም ደግሞ ሕዝቡ ከትግሉ ሸሽቶ ነበር:: ከዚያ በኃላ ሕዝቡን ወደ ትግሉ የማምጣት ሥራ መስራት ነበረብን በመሆኑም:-ሕዝቡ ላይ የሰፈረውን የፍርሐት ቆፈን መግፈፍ ስለነበር ተስፋ እንዲያጣ ገዥው ፓርቲ የራሱን ሥራ ሰርቶ ስለነበር እነዚህን ሁኔታዎች ለመቀየር በአደረግናቸው ስብሰባዎች የ97 ቱን ዓ.ም የሚመስሉ ሁኔታዎች ታይተ ዋል::

ሕዝቡ በ97 ዓ.ም የነበረው ስሜት ላይ ደርሷል ተብሎ በድፍን መናገር ባይቻልም አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቱ በመነሳት እንዲታገል ከመድረክ ጋር ከፍተኛ አስተዋፆኦ አድርገናል:: ስለዚህ ያደረግናቸው ስብሰባዎች ሕዝቡን ወደ ትግሉ በማምጣት ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: በመሆኑም በርግጠኝነት መድረክ ያሸንፋል::

***ፅናት:-*** *ወ/ሪት ብርቱካን ገዥው ፓርቲ እንዳሻው በሚጠቀምበት የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ታይተው ነበር::ይሄ ደግሞ ከጤንነታቸው መታወክ ጋር በተያያዘ ሕዝቡን ብዥታ ውስጥ ሊከት ይችላል:: ስለዚህ እርሶ ምን አስተ ያየት አለዎት?*

**አቶ አንዱአለም:-** ባለን መረጃ መሠረት ወ/ሪት ብርቱካን በቂ ሕክምና እያገኘች አይደለም:: አሁንም በሕመም ላይ ትገኛለች:: ከሁሉ የሚያሳዝነው ሽማግሌም የሐይማኖት አባትም እያጣን በመሆኑ ነው:: መሪ ማጣት ተጀምሯል:: አሁን ደግሞ የሚከበር የሐገር ሽማግሌና የሐገር መሪ እያጣን ነው:: ፓስተር ዳንኤል ከፈቃዷ ውጭ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እንድትታይ ተደርጓል::በድጋሚ መብታ እንዲጣስ ነፃነቷ እንዲገሰስ አስተዋፆ አድርገዋል:: በሌላ መልኩ በቴሌቭዥን ታየች ማለት ጤንነቷ ተጠብቋል ማለት አይደለም:: የውስጥ ሕመምና ስቃይ በቪዲዮ የሚታይ አይደለም:: በመሳሪያ ተፈትሾ እንጂ! ያቀረቡት ብሮግራም የሚያሳየው ተራ የፓለቲካ ኘሮቦጋንዳ መሆኑን ነው:: አሁንም እሷ ችግር ውስጥ ነው ያለችው:: አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኗ ሊሰለፍ ይገባል::



*አቶ አንዱአለም አራጌ*

***ፅናት:-*** *የመድረክ አመራሮች ለሥራ ወደ አሜርካ ሄደዋል የአመራር ክፍተት እንዳይፈጠር ምን ተደርጓል?*

**አቶ አንዱአለም:-** መድረክ የ8 ፓርቲዎች ስብስብ ነው:: የፓርቲው ቁጥር የአመራሩን ብዛት ያሳያል:: የሄዱት አራት አመራሮች ናቸው:: ሌላው አገር ውስጥ ይገኛል ስለዚህ ሥራው በተጠናከረ ሁኔታ እየተሰራ ነው:: በውጭ አገር የሚሰራው ሥራም የመድረክ ነው:: እና የሚያሰጋን ነገር የለም::

***ፅናት:-*** *የመድረክ አመራሮች ለሥራ ወደ አሜርካ ሄደዋል የአመራር ክፍተት እንዳይፈጠር ምን ተደርጓል?*

**አቶ አንዱአለም:-** መድረክ የ8 ፓርቲዎች ስብስብ ነው:: የፓርቲው ቁጥር የአመራሩን ብዛት ያሳያል:: የሄዱት አራት አመራሮች ናቸው:: ሌላው አገር ውስጥ ይገኛል:: ስለዚህ ሥራው በተጠናከረ ሁኔታ እየተሰራ ነው::

***ፅናት:-*** *በመጨረሻ «ዝም አንልም » በሚል የሚንቀሳቀሱና ከፓርቲው በሥነሥርዓት ጉድለት የተወገዱ ጥቂት ግለሰቦች ጠቅላላ ጉባኤ እንጠራለን ብለው ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል:: እርሶ በዚህ ጉዳይ ምን አስተ ያየት አለዎት ?*

**አቶ አንዱአለም:-** ዋናው ነገር ያለፉትን ማስታወስ ያስፈልጋል:: ከ97 በፊት ኢህአዴግ ጠንካራ ተቃዋሚ አጣሁኝ እያለ እሮሮ ሲያሰማ ነበር:: በ97 ቅንጅት ተ ጠናክሮ ሲወጣ ብርክ ያዘው:: በመሆኑም ቅንጅትን በማፍረስ ነው የተጠመደው:: ለምሳሌ ኦብኮን የተወሰኑ ግለሰቦችን በመያዝ የማፍረስ ሙከራ ተደርጉበታል:: ይሄ የሚያሳየው የኢህአዴግን አፍራሽ አካሄድ ነው:: መድረክ ተጠናክሮ ሲወጣ ግን ሌላ ብርክ ውስጥ ገብቷል:: ስለዚህ ከዚህ በፊት ሲያደርግ የነበረውን ነው:: ተቃዋሚዎችን የጥፋት ኃይል ይላል እንጂ እራሱ ኢህአዴግ የጥፋት ኃይል ነው:: በምርጫ ማሸነፍ እንደማይችል ስለሚያውቅ ተቃዋሚዎችን አደናግሮ ማሸነፍ ይፈልጋል::

እንግዲህ ከዚህ በፊት ከአንድነት ፓርቲ በሥነሥርዓት ጉድለት የተሰናበቱ አራት ወጣቶች የግቢ በር ሲሰብሩ አመልክተን መልስ አልተሰጠንም ነበር:: የአዲስ አበባ መስተዳድርን ለሻማ መብራት ለማድረግ ስንጠይቅ ትብብር አድረገውልን አያውቁም:: አሁን ደግሞ ማህተም ፊርማ ሕጋዊ መጠሪያ የሌላቸው ሰዎች ስብሰባ ሲጠሩ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል::

ይሄ እንግዲህ ኢህአዴግ ሌላ ተቃዋሚ ዎች ጠንክረው እንዳይወጡ ለማድረግ ወደ ኋላ የማይል ነው:: ትልቁ ጥላቻው ጠንካራ ፓርቲ ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ወገን ሊቋቋመው ይገባል:: ከጥቂት አምባገነኖች ጋር በመተባበር ሠላም ማምጣት አይቻልም:: ኢህአዴግ አሁን እየተከተ ለው ያለው መንገድ ኢትዮጵያን ይጎዳል ፣ተ ቃዋሚዎችን ይጎዳል ከሁሉም በላይ ግን እራሱን ኢህአዴግን ይጎዳል:: ስለዚህ ከዚህ ድርጊቱ እንዲታቀብ እናሳስበዋለን::

**መድረክን ይምረጡ!!**



# መድረክ ሲያሸንፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!!